8ኛ ዓመት ቁጥር 15
8th Year No. 15

ባህር ዳር ነሐሴ 30 ቀን 1995 ዓ/ም
Bahir Dar, Sept. 5th, 2003

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት

ዝክረ ህግ
ZIKRE HIG

Of the Council of the Amhara National Regional State in the Federal Democratic Republic of Ethiopia

በአማራ ብሔራዊ ክልል ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

Issued under the auspices of the Council of the Amhara National Regional State

✉ 1324
ያንዱ ዋጋ ብር 2.98
Unit price ----------

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር 89/1995 ዓ/ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ኤች.አይ.ቪ.ኤድስ መከ/መቆ/ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ

Contents

Proclamation No. 89/2003
The Amhara National Regional State HIV/AIDS Prevention and control council Establishment (Amendment) proclamation No. 89/2003.

አዋጅ ቁጥር 89/1995 ዓ.ም
የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከ/መቆ/ምክር ቤት ማቋቋሚያ አዋጅን ለማሻሻል የወጣ አዋጅ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት የኤች.አይ. ቪ. ኤድስ መከ/መቆ/ ም/ቤትን በተለይም የሴክሬታሪያቱን ጽ/ቤት አሠራር ቀልጣፋና ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ አደረጃጀቱን ለጉዳዩ አግባብነት ካለው የብሔራዊ ክልሉ ጤና ጥበቃ ቢሮ ጋር ማስተባበርና በሥራ እንዲደጋገፉ ማድረግ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ምክር ቤት በክልሉ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 49 ንዑስ አንቀጽ 3/1/ መሠረት ይህንን አዋጅ አውጥቷል::

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ «የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኤች. አይ. ቪ. ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ም/ቤት ማቋቋሚያ አዋጅ ማሻሻያ አዋጅ ቁጥር 89/1995 ዓ/ም» ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

Proclamation No. 89/2003

A proclamation to provide for the Amendment of the Amhara National Regional State HIV/AIDS Prevention and Control Council Establishment Proclamation.

WHEREAS, it has been found necessary to coordinate the organization of the Amhara National Regional State HIV/AIDS Prevention and Control Council with the National Regional Health Bureau of having relevancy to the matter and to cause them to back up each other operationally, especially with a view to making the performance of the office of the secretariat expeditious and more effective;

NOW, THEREFORE, the Council of the Amhara National Regional State, in accordance with Article 49 sub-Article 3/1/ of the Regional constitution, hereby issues this proclamation.

1. Short Title

This proclamation may be cited as "The Amhara National Regional State HIV/AIDS Prevention and Control Council Establishment (Amendment) proclamation No. 89/2003."

2. ማሻሻያ

የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የኤች.አይ.ቪ ኤድስ መከላከያና መቆጣጠሪያ ምክር ቤት ማቋቋሚያና ሥልጣንና ተግባራት መወሰኛ አዋጅ ቁጥር 73/1994 ዓ/ም እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

ሀ. የአዋጁ አንቀጽ 12 ንዑስ አንቀጽ 3 ተሰርዞ በሚከተለው አዲስ ንዑስ አንቀጽ 3 ተተክቷል፡፡

3. የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ ኃላፊ የቦርዱ ሰብሳቢ ሲሆን የሴክሬታሪያቱ ኃላፊ የቦርዱ አባልና ፀሐፊ በመሆን ያገለግላል፡፡

ለ. በአዋጁ አንቀጽ 13 ከንዑስ አንቀጽ 14 ቀጥሎ አዲስ ንዑስ አንቀጽ 15 ገብቷል፡፡

15. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 14 ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ጤና ጥበቃ ቢሮ ለኤች.አይ. ቪ. ኤድስ መከ/መቆ/ም/ቤት አላማ መሳካት የሴክሬታሪያቱ ሥራ የሰመረ እንዲሆን አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፡፡ ዝርዝሩ አዋጁን ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ ይወሰናል፡፡

ሐ. የአዋጁ አንቀጽ 18 ንዑስ አንቀጽ 1 ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከተው ተጨማሪ ድንጋጌ አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 ሆኖ ገብቷል፡፡

2. የዞኑ ጤና ጥበቃ ዴስክ ኃላፊ የዞኑ የሥራ አመራር ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን ይሠራል፣ የዞኑን የኤች. አይ. ቪ. ኤድስ መከላከያና ቁጥጥር ሥራዎች ማስተባበሪያ ጽ/ቤት ይደግፋል፡፡

መ. የአዋጁ አንቀጽ 23 ንዑስ አንቀጽ 1 ሆኖ ከዚህ በታች የተመለከተው ተጨማሪ ድንጋጌ አዲስ ንዑስ አንቀጽ 2 በመሆን ገብቷል፡፡

2. የወረዳው ጤና ጥበቃ ጽ/ቤት ኃላፊ የወረዳው ሥራ አመራር ኮሚቴ ሰብሳቢ በመሆን ያገለግላል፣ ወረዳ አቀፉን የኤች.አይ.ቪ. ኤድስ መከላከልና ቁጥጥር ሥራዎች ጽ/ቤት ይደግፋል፡፡

2. Amendment

The Amhara National Regional State HIV/AIDS prevention and control council Establishment and Determination of its powers and Duties Proclamation No. 73/2002 is hereby amended as follows.

a. Sub-Article 3 of Article 12 of the proclamation is hereby deleted and replaced by the following new sub-Article 3.

3. The Head of the Amhara National Regional State Health Bureau shall be chairperson of the Board and the person in charge of the secretariat shall serve as a member and the secretary of the Board.

b. Following sub-Article 14 of Article 13 of the proclamation a new sub-Article 15 is hereby inserted.

15. Without prejudice to the provision of sub-Article 14 of this Article, the Amhara National Regional State Health Bureau makes the necessary support in order for the activity of the secretariat to progress as to realization of the objective of HIV/AIDS Prevention and Control Council. Particulars shall be determined by a directive to be issued following this proclamation.

c. Article 18 of the proclamation becomes sub-Article 1, and the additional provision indicated herein under is inserted being a new sub-Article 2.

2. The Head of the Zonal Health Desk serves as a chairperson of the management committee and supports the Coordination Office of the Zonal HIV/AIDS Prevention and Control activities.

d. Article 23 of the proclamation becomes sub-Article 1, and the additional provision indicated herein under is inserted being a new sub-Article 2.

2. The Head of the Woreda Health Office serves being a chairperson of the Woreda Management Committee and supports the Coordination Office of the Worda-wide HIV/AIDS Prevention and Control activities.

3. **አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ**
ይህ አዋጅ በክልሉ ዝክረ ሕግ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

ባህር ዳር
ሐምሌ 1 ቀን 1995 ዓ/ም

ዮሴፍ ረታ
የአማራ ብሔራዊ ክልል
ፕሬዚዳንት

3. **Effective Date**
This Proclamation shall come into force as of the date of its publication in the Zikre Hig Gazeta of the Region.

Bahir Dar
The 8th Day of July 2003,

Yosef Retta
President of the Amhara
National Region.